የጎንደር ደብረ ኃይል ወደብረ ጥበበ በአታ ለማርያም ካቴድራል ሰንበት ትምህርት ቤት

የንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ትምህርት



አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ግንቦት ፲፪

ማውጫ

ንጽጽራዊ ነገረ መለኮት (Comparative Thelology) 3

የንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ትምህርት ጥቅም 3

በንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ትምህርት ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች 3

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የይሁዲነት እምነት ልዩነትና አንድነት 3

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የቡድሂዝም ልዩነት 3

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የካቶሊክ ልዩነት 4

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አንድነትና ልዩነት (Oriental Orthodox Vs Eastern Orthodox) 4

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የእስልምና እምነት ልዩነትና አንድነት 5

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የግኖስቲኮች ልዩነት 5

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የቅባት እምነት ልዩነትና አንድነት 5

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የጸጋ እምነት ልዩነት 6

የዮሐንስ ተዓቃቢ ክሕደት 6

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የፕሮቴስታንት እምነት ልዩነት 6

ንጽጽራዊ ነገረ መለኮት (Comparative Thelology)

ንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ማለት የተለያዩ ሃይማኖቶች በተለያዩ ጉዳዮች ያላቸውን እሳቤና አስተምህሮ ማነጻጸር ማለት ነው። ይኸውም ለምሳሌ ስለመገለጥ፣ ስለዓለም አፈጣጠር፣ ስለመኖር ምክንያት፣ ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወትና ስለመሳሰሉ ጉዳዮች የተለያዩ ሃይማኖቶች ያላቸውን እይታ ማነጻጸር ነው።

የንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ትምህርት ጥቅም

- ✓ የራሳችንን ሃይማኖት አስተምህሮ ጠንቅቆ ለመረዳት
- ✓ የእኛ ሃይማኖት ከሌሎች ቤተ እምነቶች የሚለይበትን ለመረዳት
- ✓ ከሐሰተኛ ክስ ለመዳን
- ✓ የእኛ ሃይማኖት ከሌሎች ቤተ እምነቶች የሚመሳሰልበትን ጉዳይ ለመለየት

በንጽጽራዊ ነገረ መለኮት ትምህርት ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች

- ➢ የሌላ እምነት ሰዎች የሚናገሩትን ነገር ሳናጣራ ወይም በጥላቻ የማይሉትን እንደሚሉ አድርገን መናገር አይገባንም።
- ➢ በብዙ ነገር ከሌሎች ቤተእምነቶች የምንለያይ ቢሆንም በአንዳንድ አስተምህሮዎች ልንመሳሰል ስለምንችል በጅምላ ከመፈረጅ ይልቅ የምንመሳሰልበትንና የምንለያይበትን ነገር አጥርቶ መለየት ያስፈልጋል።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የይሁዲነት እምነት ልዩነትና አንድነት

አስተምህሮ	ይሁዲነት	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ይቀበላሉ	አዎ	አዎ
እግዚአብሔርን በአካል አንድ ነው ይላሉ	አዎ	አንልም
የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ይቀበላሉ	አይቀበሉም	እንቀበላለን
ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ አንድያ ልጅ ነው ብለው ያምናሉ	አያምኑም	አዎ
የእግዚአብሔር መሢሕ እስከ አሁን (2018 ዓ.ም) ድረስ አልተወለደም ይላሉ	አዎ	አንልም
እግዚአብሔር በአካል ሦስት በመለኮት አንድ ነው ብለው ያምናሉ	አያምኑም	አዎ

ከይሁዲነት እምነት ተከታዮች ጋር በምናደርጋቸው ምልልሶች (ተዋሥኦዎች) ብሉይ ኪዳንን መሠረት አድርገን እንነጋገራለን። ምክንያቱም እኛም እነርሱም ብሉይ ኪዳንን እንቀበላለንና ነው። በብሉይ ኪዳን መሢሑ እንደሚለወለድ ትንቢት ተነግሯል። እኛ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶዎች ያ ትንቢት በክርስቶስ ተፈጽሟል እንላለን። ይሁዲዎች ግን መሢሑ ክርስቶስ አይደለም ይላሉ።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የቡድሂዝም ልዩነት

አስተምህሮ	ቡድሂዝም	ኦርቶዶክስ
ሰው ከሞተ በኋላ ሌላ ፍጥረት ሆኖ ይወለዳል (Reincarnation)	አዎ	አንልም
ዓለማትን የፈጠረ ከሁሉ በላይ የሆነ አንድ አምላክ አለ	አይሉም	አዎ

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የካቶሊክ ልዩነት

አስተምህሮ	ካቶሊክ	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
የኬልቄዶን ጉባኤን ይቀበላሉ	አዎ	አንቀበልም
ክርስቶስን አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ይላሉ	አይሉም	አዎ
ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ይላሉ	አዎ	አንልም
የሃይማኖትን ሥርዓት፣ ቀኖና፣ አስተምህሮ ለመወሰን ፓትርያርኩ የበላይ ባለሥልጣን ነው	አዎ	ፓትርያርኩ ክቡር ቢሆኑም ሊሳሳቱ የሚችልና ንግግሩ በአስተምህሮ የሚመዘን ነው
መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም የሠረጸ ነው	አዎ	መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ የሠረፀ ነው
ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ይቀበላሉ	አዎ	አዎ
ቁስ ያላገባ ድንግል መሆን አለበት ይላሉ	አዎ	ያገባም ቁስ መሆን ይችላል። ያላገቡ መነኰሳትም የቅስና ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል
የኒቅያ ጉባኤን፣ የኤፌሶን ጉባኤንና፣ የቍስጥንጥንያን ጉባኤ ይቀበላሉ	አዎ	አዎ

ከካቶሊኮች ጋር በሚኖረን ውይይት ብሉይ ኪዳንን፣ ሐዲስ ኪዳንንና የሦስቱ ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ውሳኔዎችን መሠረት አድርገን መወያየት እንችላለን። ካቶሊኮች ድንግል ማርያም ኀይል አርያማዊት ናት ይላሉ እየተባለ የሚነገረው ንግግር የተሳሳተና መሠረት የለሽ ነው። በካቶሊክ አስተምህሮ ንስሓውን ሳይጨርስ የሞተ ሰው ንስሓውን የሚጨርስበት መካነ ንስሓ (Purgatory) አለ ይላሉ። እኛ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶዎች ግን በነፍስ ሁለት ዓለማት ብቻ እንጂ ሦስተኛ አለ አንልም።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አንድነትና ልዩነት

(Oriental Orthodox Vs Eastern Orthodox)

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ የሚባሉት በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተለዩ ናቸው። እነዚህም የግሪክ ኦርቶዶክስ፣ የሩሲያ ኦርቶዶክስ፣ የዩክሬን ኦርቶዶክስና የመሳሰሉት ናቸው። ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሚባሉት ደግሞ የኢትዮጵያ፣ የግብጽ፣ የሶርያ፣ የህንድ፣ የአርመንና የኤርትራ አብያተ ክርስቲያን ናቸው።

አስተምህሮ	የምሥራቅ ኦርቶዶክስ	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ያምናሉ	አዎ	አዎ
መንፈስ ቅዱስን ከአብ ብቻ የሠረጸ ነው ይላሉ	አዎ	አዎ
ክርስቶስን አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ይላሉ	አዎ	አንልም
የኬልቄዶን ጉባኤን ይቀበላሉ	አዎ	አንቀበልም
ለቅዱሳን የጸጋ ክብር ይገባቸዋል ይላሉ	አዎ	አዎ

የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ልዩነት ብዙው በነገረ ክርስቶስና በምሥጢረ ሥላሴ ነው። ምሥጢራትን በመፈጸም፣ ቅዱሳንን በማክበርና በመሳሰሉት ጉዳዮች የአፈጻጸም ልዩነቶች ቢኖሩም በብዙ መልኩ እንመሳሰላለን።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የእስልምና እምነት ልዩነትና አንድነት

አስተምህሮ	እስልምና	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
በፈጣሪ መኖር ያምናሉ	አዎ	አዎ
ገነትና ሲኦል እንዳሉ ያምናሉ	አዎ	አዎ
ነቢያት ከፈጣሪ የተላኩ እንደሆኑ ይቀበላሉ	አዎ	አዎ
መጽሐፍ ቅዱስን ይቀበላሉ	አይቀበሉም	አዎ
ቁርዓንን ይቀበላሉ	አዎ	አንቀበልም
ምሥጢረ ሥላሴን ይቀበላሉ	አይቀበሉም	አዎ
ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት አንዱ ነው እንጂ አምላክ አይደለም ይላሉ	አዎ	አንልም
መሐመድን እንደ ነቢይ ይቀበሉታል	አዎ	አንቀበልም
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው ይላሉ	አይሉም	አዎ

ከእስልምና እምነት ጋር በሚኖር ክርክር (ተዋሥኦ) የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትና የሥላሴን ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ገልጾ ማሳየት ይቻላል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳንከራከራቸው አስቀድመው መጽሐፍ ቅዱስ ተበርሏል ስለሚሉና እኛ ደግሞ ቁርዓንን ከተለያዩ መጻሕፍት የተወጣጣ መጽሐፍ እንጂ ከፈጣሪ የተገለጠ ነው ብለን ስለማናምን ለመከራከሪያ የሚሆን የጋራ መጽሐፍ የለንም።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የግኖስቲኮች ልዩነት

አስተምህሮ	ግኖስቲኮች	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቁሳዊውን ነገር ሁሉ እንደ ርኩስ ሲቆጥሩ መንፈሳዊውን ዓለም ደግሞ እንደ ቅዱስ ይቆጥራሉ	አዎ	ፍጥረት ሁሉ በተፈጥሮው መልካም ነው
መዳን በእምነትና በሥራ ሳይሆን በዕውቀት ይገኛል ይላሉ	አዎ	መዳን በማመንና መልካም ሥራን በመሥራት ነው

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የቅባት እምነት ልዩነትና አንድነት

አስተምህሮ	ቅባት	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
የክርስቶስ ሥጋ የባሕርይ አምላክ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ (ክብር) ሆኖት ነው ይላሉ	አዎ	አንልም
ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ ማለት ነው	አዎ	አዎ
ሥጋ የባሕርይ አምላክ የሆነው ከቃል ጋር በመዋሐዱ ነው ይላሉ	አይሉም	አዎ
የሐዋርያት ጾም የሚገባው ጰራቅሊጦስ በዋለ በስምንተኛው ቀን ነው ይላሉ	አዎ	አንልም የሐዋርያት ጾም በጰራቅሊጦስ ማግስት ይጀምራል
የነቢያት ጾምን የሚጀምሩ ከህዳር 19 ጀምረው ነው	አዎ	ህዳር 15 ይጀመራል

ቅባቶች በጊዜ ተዋሕዶ አብ ቀባኢ፣ ወልድ ተቀባኢ፣ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ይላሉ። እኛ ተዋሕዶዎች ግን ሦስቱ አካላት በማክበር አንድ ናቸው ለሥጋ ክብር (ቅብዕ) መሆን ግን በተለየ ለቃል ይነገራል እንላለን።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የጸጋ እምነት ልዩነት

አስተምህሮ	ጸጎች	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ክርስቶስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ እንደ እኛ የጸጋ ልደትን ተወልዷል ስለዚህ ሦስት ልደት አለው ይላሉ።	አዎ	አንልም። ለክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ ድኅረ ዓለም ከድንግል ማርያም እንደተወለደና ሁለት ልደታት እንዳለው እናምናለን እንጂ

የዮሐንስ ተዓቃቢ ክሕደት

የሐንስ ተዓቃቢ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ እየራሳቸው ቃል፣ ልብ፣ እስትንፋስ አላቸው ይል የነበረ ከሓዲ ነው። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ ግን አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ሆነው በአንድ ህልውና በአንድ መለኮት ተገናዝበው ይኖራሉ እንላለን። የዮሐንስ ተዓቃቢ ክሕደት የማይገነዛዘቡ ሦስት መለኮት አሉ የሚል ነው። እኛ ግን ሦስቱ አካላት በከዊን አማካኝነት በመለኮት ይገናዘባሉ እንላለን። አንዳንዶች ክርስቶስን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ የሆነ ስለሆነ ለወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ የማይገናዘብ ባሕርይ ከሌለው በስተቀር አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ ስለሚያሰኝ የወልድ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ የተለየ የራሱ ባሕርይ አለው ይላሉ። አንድ ባሕርይ መባሉም የሦስቱ ባሕርይ ስለተመሳሰለ እንጂ ስለሚገነዛዘብ አይደለም ይላሉ። እኛ ግን ባሕርየ ሥላሴ በቃል ከዊን ሰው ሆነች ስለምንል አምላክ ሰው ሆነ ባልን ጊዜ አብና መንፈስ ቅዱስ ሰው ሆኑ አያሰኝም እንላለን።

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የፕሮቴስታንት እምነት ልዩነት

አስተምህሮ	ፕሮቴስታንት	ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
የቅዱሳንን አማላጅነት አይቀበሉም	አዎ	የቅዱሳንን አማላጅነት እንቀበላለን
66 ክፍል ያለው መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ እንጂ ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን አይቀበሉም	አዎ	ቅዱስ ትውፊትንና ሌሎችንም ቅዱሳት አዋልድ መጻሕፍትን እንቀበላለን
በእምነት ብቻ መጽደቅ ይቻላል ይላሉ	አዎ	ለመጽደቅ እምነትም መልካም ሥራም ያስፈልጋሉ
ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ የቤዛነት ሥራውን ከፈጸመ በኋላም እየማለደ ይኖራል ይላሉ	አዎ	ከዕለተ ዓርብ ወዲህ አይማልድም እንላለን

ቃላት በተለያዩ ቤተ እምነቶች የወከሉት ሐሳብ ልዩ ልዩ ሊሆን ስለሚችል ጠንቅቆ መለየት ያስፈልጋል። ሃይማኖት ከአመክንዮ በላይ ቢሆንም የተለያዩ ቤተ እምነቶችን ትምህርት ስናነጻጽር የአመክንዮ ፍልሰት (Logical Fallacy) መሥራት አይገባንም።